11ኛ አመት ቁጥር 26
11th Year No 26

ባህር ዳር ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 21st, July 2006

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር<br>Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ 312<br>P.o. Box |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 41/1998 ዓ.ም | Regulation No.41/2006 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በከተማ ክልል ውስጥ ከተፈቀደ ፕላን ውጭ የተሰሩ ግንባታዎች ቅጣት ታሪፍ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State the Penalty Tariff Against Constructions undertaken out of Approved plans in the Urban Centers Amendment, Council of Regional Government Regulation. |

### ደንብ ቁጥር 41/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በከተማ ክልል ውስጥ ከተፈቀደ ፕላን ውጭ የተሰሩ ግንባታዎች ቅጣት ታሪፍን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

### REGULATION NO.41/2006

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO AMEND THE PENALTY TARIFF AGAINST CONSTRUCTIONS UNDERTAKEN OUT OF APPROVED PLANS IN THE URBAN CENTERS OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

በክላላችን የሚገኙ ከተሞች በውስጣቸው የሚካሄደውን ማናቸውንም ህገ-ወጥ ግንባታ መቆጣጠር አይነተኛ ተግባራቸው መሆኑ ቢታወቅም ቀደም ሲል ወጥቶ በሥራ ላይ በዋለው የማዘጋጃ ቤቶች ገቢ ማሳደጊያና የከተሞች ሚና ማጐልበቻ ክልል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 12/1992 ዓ.ም ሥር የተደነገገው ያልተፈቀዱ ግንባታዎች ቅጣት ተመን ካስተማሪነቱ ይልቅ በገቢ ማዳበሪያነቱ ላይ ያተኮረ መስሎ ከመታየቱ የተነሣ ይህንኑ መርምሮ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

WHEREAS, in spite of the fact that the prevention of illegal constructions in their respective administrative jurisdictions is known to be the typical duty of urban centers in our Regional State, the penalty rate provided for under the existing municipalities' Revenue-fostering and urban Role-enhancement Regional Executive Committee Regulation No 12/1999 against unauthorized constructions is considered as focusing on revenue-boosting rather than correcting misdeeds and it has thus been necessary to examine and amend same thereof;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

Now, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, by virtue of powers vested in it under Article 58 sub-Art.7 of the revised Regional Constitution, hereby issues this regulation.

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ከተፈቀደ ፕላን ውጭ የተሰሩ ግንባታዎች ቅጣት ታሪፍ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 41/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 1. Short Title

This regulation may be cited as "The Amendment of Penalty Tariff against Constructions out of approved plans Council of Regional Government Regulation No. 41/2006."

## 2. ማሻሻያ

በአማራ ብሔራዊ ክልል የማዘጋጃ ቤቶችን ገቢ ለማሳደግና የከተሞችን ሚና ለማጐልበት ከወጣው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 12/1992 ዓ.ም ጋር በተያያዘው 12ኛ ሠንጠረዥ ተራ ቁጥር 2 ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ-ሐ የተመለከቱትና ከተፈቀደ ፕላን ውጭ በከተሞች ክልል ውስጥ የሚሰሩትን ግንባታዎች ለመቅጣት የተወሰኑት የቅጣት ተመኖች በዚህ ደንብ እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፦

ሀ. ግንባታው ከፍተኛ ለውጥን ያስከተለ ሆኖ ሲገኝ ቅጣቱ የተለዋጭ ግንባታውን ወጪ 8% ይሆናል።

ለ. ለውጡ መካከለኛ ሆኖ ሲገኝ ቅጣቱ

## 2. Amendments

Referring to the Executive Committee Regulation No. 12/1999 issued to maximize the revenue of municipalities and to enhance the role of urban centers in the Amhara National Regional State, the penalty rates determined against constructions out of authorized plans indicated under schedule XII, No. 2 (A-C) attached therein are hereby amended as follows:

A. Where the construction is proven to have caused major alteration, the penalty for such an act shall be 8% of the varied construction expense.

B. Where the alteration is found to be of a medium character, the penalty for such an act shall be

የተለዋጭ ግንባታውን ወጪ 5% ይሆናል።

ሐ. ለውጡ ዝቅተኛ ወይም መጠነኛ ከሆነ ቅጣቱ የተለዋጭ ግንባታውን ወጪ 3% ይሆናል።

## 3. ስለ ለውጦቹ አይነትና ይዘት

ከተፈቀደ ፕላን ውጭ የሚከናወኑ ግንባታዎችን አስመልክቶ ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ወይም መጠነኛ ለውጦች የሚመዘኑበትን የማስፈፀሚያ መመሪያ የክልሉ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሊያወጣ ይችላል።

## 4. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር

ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ርዕሰ መስተዳድር

5% of the varied construction expense.

C. Where the alteration is minor and thus of a sizable nature, the penalty, in that case, shall be 3% of the varied construction expense.

## 3. Kind and nature of the Alterations

The Regional Bureau of Works and Urban Development may issue an Executive directive on the standardization of major, medium and minor alterations hereof , with regard to constructions undertaken in violation of authorized plans.

## 4. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar

This 21st day of July, 2006

Ayalew Gobezie

Head of Government of the Amhara

National Regional State